# የሃሳብ መንገድ ጉድ ሳይሰማ

ጉድ ሳይሰማ

ጉድ ሳይሰማ መስከረም አይጠባም እንዲሉ አጀብ አሰኝቶን የተጀመረው 2007 ጉድ አሰኝቶን ተጠናቋል። በሌላ ሃያሏ ዩኤስ አሜሪካ መዲና ዋሽንግተን ዲሲ የሚገኘውን የኢትዮጵያን ኢንባሲ ኢትዮጵያዊያን የለውጥ አቀንቃኞች መስከረም 26 /2007 ዓም ለደቂቃዎች ሲቆጣጠሩ የኢምባሲው የጥበቃ ሃላፊ ተኩስ በመክፈት ለትእይንቱ ድምቀጥ ከመስጠት ባሻገር የህወሃት ሰዎች ድንቁርና ድንበር የማያግደው እርቀት የማይገድበው መሆኑን አሳይቶናል። የህወሃት ህዝባዊ ወያኔ ሃርነት ታጋይ የአለም የፖለቲካ መአከል በሚባለው ዋሽንግተን ዲሲ ውስጥ ቁጭ ብሎ የ ጌትነት ካባ ደርበው ልምጭ ባልያዙ ያገሩ ልጆች ላይ አነጣጥሮ ሲተኩስና ጥይቱ ሲደነብሽበት አይተናል። በ48 ሰአታት ውስጥ አመሬካን ለቆ እንዲወጣ ተወስኖበት ጓዙን ጠቅልሎ መውጣቱንም ተከታትለናል። በዚህም ሳቢያ የህወሃት ካምፕ የነበረው ሃዘን ቁጭትና እልህ እንዲሁም ቀለብ በሚሰፈርላቸው አገልጋይ ወገኖች የነበሩ ማላዘን አንዳመት ብቻ ነውና አንረሳውም። የህወሃት ታጋዮች የነጻነት አርበኛውን አንዳርጋቸው ጽጌን ከየመን የጸጥታ ሃይሎች በረብጣ ዶላሮች በመግዛት የዘረኝነትና የዘረፋ ስርአታቸውን ለማደላደል ቢቋምጡም ነጻነትን የተራቡ ኢትዮጵያዊያን ሁለት ወር ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ ዋሽንግተን ዲሲ ላይ ምላሽ ሰተዋል። እኛም አንዳርጋቸው ነን ያሉት ደግሞ አመቱን ሙሉ መረብን እየተሻገሩ ብረት ማንሳታቸውን ሰምተናል። የጠመንጃው ግብግብ እንዲያበቃና የሰለጠነ ፖለቲካ በሃገራችን እውን እንዲሆኑ የጣሩ ስልጡን ፖለቲካ ስልጡን ካልገባው ሃይል ጋር እንደማይሆን ተገንዝበው ነጻነት ፍለጋ ድንበር እያቋረጡ መሳሪያ አንስተዋል። ብረሃኑ ተክለያሬት እየሩሳሌም ተስፋሁንና ፍቅረማሪያም አስማማውን የመሳሰሉ ወጣቶች ነጻነት በሰላማዊ መንገድ እንደማይቻል በድርጊት ሲነገራቸው ነጻነት ፍለጋ ድንበር ሲያቋርጡ መያዛቸውን ለፍርድቤት በኩራት በመናገር ለወኔያቸው የብዙዎችን አትኩሮት አትርፈዋል።

ዋሽንግተን ላይ ጉድ አሰምቶ አመቱን ያስጀመረን 2007 ጉድ ሳይሰማ መስከረም አይጠባም የሚባለውን ቢሂል ይበልጥ ገላጭ በሆነ መልኩ ጿግሜ 6 ቀን ሞላ አስገዶምን በማሻገር ከጉድም ጉድ አሰኝቶን አልፏል። መስከረም 2008ም ጉድ ይዞ ጠብቷል። እርግጥ ነው 2007 ጉድ ያሰኘን መግቢያውና መውጫው ላይ ብቻ ሳይሆን በታህሳስ 2007 ዓም የኢትዮጵያ አየር ሃይል ሁለት አብራሪዎችእና አንድ ቴክኒሻን ኤም አይ 35 የተሰኘ ዘመናዊ ሄሊኮፕተር ይዘው መሰወራቸውና መንግስትም ኤርትራ ገቡ ሲል መግለጫ መስጠቱን የሚታወስ ሲሆን በህወሃት መንደር የደረሰው ስብራትና ቁጭት እንዲሁም ጫጫታ የሚዘነጋ አይደለም። አቶ መለስ ዜናዊ ከመሞታቸው በፊት በአንደበታቸው እንደነገሩን ብዙ ደጅ የጠኗት ተሰናባቹ ፕሬዜዳንት አቶ ግርማ ወልደጊዎርጊስ እንዲሁም ያቶ መለስን ወንበር ያለስልጣን የወረሱት አቶ ሃይለማሪያም ደሳለኝ የተማጸኗት ኤርትራ በጉዳዩ ምንም ሳትል እነሱ በሚሰጡት ፉከራ በልቦለት ወይም በካርታ ላይ ጦርነት ዘጠኝ ወራ አስቆጠሩ። የአፋራዊቷ ዲሞክራሲያዊ ግንባር አርዱፍ በ2004 ዓም በአፋር ኤርታሌ አካባቢ የአውሮፓ ቱሪስቶችን ከማገቱ ጋር ተያይዞ የገር መከላከያ ሚኒስቴር ኤርትራን አጠቃው በማለት ምርኮኛ ያዝን ማለታቸውም ይታወሳል። የተናገሩትን እረስተው ከሰራዊቱም ይሁን ከሚንሻው ምርኮኛ አዘጋጅተው ሳያሳዩን ሶስት አመታት ማለፋቸውን እየታዘብን እንገኛለን።

ሻብያን ለመግጠም ለምን እንደፈሩት የሚያውቁት እነሱ ቢሆኑም የሟቹን ጠቅላይ ሚኒስቴር አቶ መለስ ዜናዊንና የቀድሞ ውን የአየር ሃይል አዛዝ ጄነራል አለምሸት ደግፌ ትንተና ዊክሊክስ ላይ ላነበበና የአሜሪካን ስቴት ዲፓርትመንት ሰነድ ለበረበረ ለስጋታቸውና በፎከሩት መጠን ወደ ድርጊት ላለመሄዳቸውም ይገለጽለታል። እርግጥ ነው ስልጣን ብቻም ሳይሆን የመረጃ ገደብ ያለባቸው የሚመስሉት አቶ ሃይለማሪያም ደሳለኝ አቶ መለስ የተናገሩትን አጠንጥነው እየሰሙ መልሰው ማስተጋባታቸውን ቀጥለዋል። አቶ ሃይለማሪያም በለመደ ምላሳቸው ግብጽን ሲያስጠነቅቁ ሰምተን በብሄራዊ ስሜት እንዳናጨበጭብላቸው የመረጃ እጥረት እንዳላባቸው ይከሰትልናል። ግብጽና ጅቡቲን መለየት ሲሳናቸው ደሞ መጨማቀቃችን የግድ ነው። ለክብራችንና ለሉአላዊነታችን ዋጋቸውን ለመክፈል ተዘጋጅተናል ብለው ብሄራዊ ስሜት መቀስቀስ የመሪ ወጉ ቢሆንም ግብጽ ታወቀናለች ብሎ መፎከር የመረጃ ክፍተቱን ከማሳየት ባሻገር ሰውዬው የስልጣን ብቻ ሳይሆን የኢንፎርሜሽን ገደብ አለባቸው የሚለውን አጥብቀን እንድናነሳ ያደርገናል። ግብጽ ላይ ለመፎከር የማያቅማሙት ኤርትራ ላይ ማቅራራታቸው የሚጠበቅ ቢሆንም ቀረርቶው ሲበዛ ግን የፍረሃት ማስታገጫ ኪኒን እየመሰለ ልምምጡን ያስታውሰናል። ኤርትራ ለኢትዮጵያ ነጻነት ሃይሎች ከለላ መስጠቷን ገሃድ ሲወጣ የአንድነት ሃይሎች መሰረታቸው ሲሰፋ በህወሃት ካምፕ የተፈጠረው ጫጫታ ከድሪጊት ይልቅ በምኞት የተሞላ መሆኑን ኢሳያስ ሞቱ የሚለውን ዜና በአዲሳባው ሪፖርተር እስከ ካርሊፎርኒያው አይጋ እንዲሁም በ እነንትና ሲዘገብ ጭምር ታዝበናል። የቀድሞው ታጋይ ሞ ላ አስገዶም የተወሰኑ አባላት አስከትሎ እጅ ሲሰጥ የጫቢያን ጦር ደምስሶ መጣ በማለት ከአጼ ፖሃንስና ከራስ አሉላአባነጋ ጋር ፎቶውን የለጠፉ የህወሃት ደጋፊዎችን ገጽ አይተን ሻብያን የመደምሰስ ምኞታቸውን አይተን ከምን የመነጨ ነው የሚለውን ልንመረምር ቢሆንም ዝርዝር ሁኔታውን ለግዜው አቆይተን ከዋናዎቹ ጉዳዮች አንዱ ሻቢያን ብናጠፋ መሳሪያ ያነሱ የተቃዋሚ ሃይሎች ድራሽ ስለሚጠፋ ተደላድለን እየዘረፍን እንቀጥላለን ከሚል ምኞት ይመነጫል። ደሃ በህልሙ ቂቤ ባይጠጣ ንጣት ይገድለው ነበር እንዲሉ ሻብያን መደምሰስም ሆነ የኢትዮጵያ ተቃዋሚ ሃይሎችን መድረሻ ማሳጣት ከሁኔታዎች ግምገማ አንጻር በጣም የረፈደ በጣም የዘገየም የማይቻልና የማይሞከርበት ደረጃላይ በመድረሱ የህወሃት ደጋፊዎች እርማቸውን እንዲያወጡ መጠየቁ

ተገቢ ይመስለኛል ። የቀድሞው መሪ መንግስቱ ሃይለማሪያም ትግላችን በተባለ መጽሃፋቸው “ወያኔን መሳሪያ ብቻ ሳይሆን ሱሪም ያስታጠቀው ሻብያ ነው“ ማለታቸውን ማስታወሱ ተገቢ ነው። ይሁንና ተአምር ተፈጥሮ እንኳን ምኞታቸው ቢሳካና ሻቢያ ቢደመሰስ የነጻነት ትግሉ ይዘገይ ይቀዘቅዝ እንደሆን እንጂ ለሃያ አንደኛው ክፍለዘመን የማይመጥኑ መንደርተኞች አገዛዝ በዘመናዊው አለም ስጋ ለብሶ አይቀጥልም።

ኢኮኖሚስቱ በአሜሪካን በክኔል ዩ ኒቨርስቲ ፕሮ ፌሰር ማእረግ ያገኙትና የወርቅ ማንኪያ ጎርሰው ይችን አለም የተቀላቀሉት በግልጽ አነጋገር ከሃብታም ቤተሰብ የተገኙት እውቀትም ብቃትም ሃብትም ምንም ሳይጎድላቸው የነጻነት ረሃብ የህዝብ በደልና ሰቆቃ ከአሜሪካ ወደ በረሃ የጠራቸው ፕሮ ፌሰር ብረሃኑ ነጋ ሃምሌ 11ቀን 2007 ዓም አርበኞቹን የመቀላቀላቸው ዜና ጉድ ያሰኘው ኢትዮጵያንም ብቻ ሳይሆን የምእራብ ዲፕሎማቶችን መንግስት ሃላፊነት ላይ የሚገኙት አሜሪካንን ጭምር መሆኑን ተገንዝበናል። እርግጥ ነው ለነገሩ እንግዳ ለሂደቱ ባዳ የማይሆኑ የአሜሪካ ባለስልጣናት መኖራቸውን መርሳት ተገቢ አይሆንም። የአሜሪካንና የኤርትራን ግንኙነት የማደሱን እንቅስቃሴ አሜሪካን ኢንባሲ ወደ አምባሳደር ደረጃ ለማሳደግ መወሰኗ የተያያዘ ባይሆን እንኳ የሚጠቅም መሆኑን አያጠያይቅም። አቶ ኤፍሬም ማዴቦ ፕሮፌሽናል የሆነ ስራቸውንና ከፍተኛ ዶላር የሚያስገኝላቸውን ገቢያቸውን ትተው ከታዳጊ ልጃቸው ተለይተው በረሃ ሲወርዱና የአንዳርጋቸውን አርማ በጋራ ሲያነሱ የነጻነቱ ወዳድ ልብ በሃሴት እንደተሞላ ሁሉ ሆዳቸው በህሊናቸው ለሚበረታ በርግጥ የተግባር እብደት ነው። ይህ ሁኔታ በዘረኛውና በዘራፊው ካምፕ የፈጠረው ሽብር ደግሞ የሞ ላ መክዳት የሚያረክሰው አይሆንም። በፕሮፌሰር ብረጋኑ ነጋ በረሃ መውረድ ተደንቀን በኤርትራ የሚገኙ መሳሪያ ያነሱ ሃይሎች የአገር አድን ንቅናቄን መስርተው የውህደት ጉዞ መጀመራቸውን በሰማን ማግስት የነጻነት ሃይሎች ደስታውን ሳያጣጥሙ የዴሚህቱ መሪና የንቅናቄው ምክትል ሊቀመንበር አቶ ሞላ አስገዶም ወደ እናት ድርጅታቸው ወደ ህወሃት መመለሱን ተነገረን። የተናደዱም ያዘኑም ከዚያም ያለፉ ለውጥ ፈላጊዎች ብዙ ቢሆኑም አቶ ሞላ አስገዶምና የሃገሪቱ የደህንነት መስሪያቤት የሚከውኑት ተግባር ትዝብትና ፌዝ እየጋበዘ ቀጠለ።

ከሞላ አስገዶም ጋር አንድ አመት የፈጀ ግንኙነት አድርገናል ያለው የሃገሪቱ የደህንነት መስሪያ ቤት በዚህ አንድ አመት የደምሂትን ሰራዊት ከማጠናከር ይልቅ ትግሉን ለማዳከም ምን ተሰራ የሚለውን መመለስ ሳይችል ቀርቷል። ፕሮፌሰር ብረሃኑ ነጋ ኤርትራ እንዲገቡ ያደረገው አንድ እኛ ነን ሌላ ግዜ ደሞ ኤርትራ ነች የሚለውን የተምጣታ መግለጫ ወደጎን ትተን ኤርትራ ለምን እንዲገቡ አደረጋቹ ለሚለው ሳያስቡ የተናገሩትና በአቅማቸው መጠን የፈበረኩት በመሆኑ ከአቅማቸው ያለፈ ጥያቄ ሲመጣ ምላሻቸው ዝምታና ሽሽት ሆኗል። ሌላው ከማሳፈር በላይ የሆነው ተግባር ደግሞ ከአቶ ሞላ ጋር ተገደው ይሁንም ፈቅደው እጃቸውን የሰጡትን ወታደሮች በየተራ በቴሌቪዥን እያቀረቡ ከመንግስት ጋር ለአንድ አመት ያህል በሚስጥር ስንሰራ ነበር የሚል መግለጫ እንዲሰጡ ማድረጋቸው የሃገሪቱ የጸጥታ ተቋም ዊክሊክስ ላይ ከተረዳነው በላይ ፍጹም ተራና ደካማ በሆኑ ሰዎች እጅ መሆኑን ይመሰክራል። እድሜ ለጁሊያን ናሳን እጅ የኢትዮጵያው የደህንነት አላፊ አቶ ጌታቸው አሰፋ አሜሪካ የግንቦት 7 መሪዎችን ከሃገሯ ካላባረረች እኛም የአሜሪካ ተቃዋሚዎችን እንረዳለን በማለት ለአሜሪናው አንባሳደር መናገራቸውን በዊክሊክስ በኩል ከተመለከትን አምስት አመታት ያለፈ ቢሆንም ሰውዬውን እና ተቋማቸውን አሁንም ካሉበት የንቃተ ህሊና ደረጃ ፈቀቅ አለማለታቸውን ተረድተናል።

ሞላ አስገዶም በግልጽ እንደተናገረው ሻቢያዎችም ጥምረቱ እንዲፈጠር በመገፋፋታቸው ፕሮ ፌሰር ብረሃኑ ነጋ ሊቀመንበር እንዲሆኑ ፍላጎት በማሳየታቸው በሌላም በኩል የደህሚት መሪዎች ሲናገሩ እንደሰማነው አቶ ሞላ የድርጅቱ ሊቀመንበር ሆነው የመቀጠሉ ጥያቄ በግምገማ ድረስ በመግባቱ በኩርፊያ እጅ ለመስጠት እንደወሰነም እንገነዘባለን። ይህ ከሆነም ዘንዳ ሞ ላ አስገዶም ግንኙነት ሲፈጥር የሃገሪቱ የደህንነት መዋቅር ሞ ላ ብቻውን ሊመጣ ይችላል ወይስ ከሰራዊት ጋር ብቻውን ከመጣ እንዴት እናስተናግደው ከሰራዊትስ ጋር ከመጣ እንዴት እንቀበለው ቢደረስበትና ቢቀርስ ቢታሰር ወይ ቢገደልስ ምን እንበል እንዴትስ ለህዝብ እናቅርበው የሚለውን ከመነሻው ያልተዘጋጁበት ብቻም ሳይሆን ሞላ እጃቸው ከገባ በኋላም ትንሽ ብቻ አእምሯቸውን ቢያሰሩ የለውጥ ፈላጊውን ካምፕና በኤርትራ በኩል በሚደረገው ትግል ላይ ከፍተኛ ውዥንብር እንዲሁም ጥቂት መንገጫችገጭ ባስከተሉ ነበር። ሰላማዊ ሰዎችን ለመወንጀል ታክሲ ውስጥ ፈንጂ እያጠመዱ ንጹሃንን የሚገድሉት የኢትዮጵያ የደህንነት መስሪያቤት ሃላፊዎች ሞላ አስገዶም ከነሰራዊቱ እንደገባም ለሱዳን የጸጥታ ሰራተኞች እንደለመዱት ጥቂት በመክፈል ሞላን በመግደል ወይም አፍኖ በመውሰድ በመሰወርና መግለጫ በመስጠት አሁን በቀናት የሞተውንና እነርሱ ላይ ባርቆ ያለፈውን የሞላ አስገዶምን ሁኔታ በለውጥ ፈላጊው ካምፕ የውዥምብር አርእስት በማድረግ ትንፋሽ መሳብ በቻሉ ነበረ። በቃላት የሚኳኳለውንና ወይንም በብቃት የኮሰሰ የብሄራዊ መረጃና የፌደራል ፖሊስ የጸረ ሽብር ግብረሃይል ከመከላከያ ሰራዊት ጋር በመተባበር ኤርትራ መሽገው ኢትዮጵያን ሰላም የሚያውኩ ሃይሎች ላይ እርምጃ ወሰደ ደመሰሰ ሞላ አስገዶም ሲገደል ወይም ሲማረክ ሌሎቹ ተበታትነው አምልጠዋል በማለት ልቦለድ ቢያቀነባብሩ ወይንም ሞላ አስገዶምን አፍነው ዝምታን ቢመርጡና ሻብያ ገደለው ቢሉ ይፈጠር የነበረው ውዥንብር ቆም ብሎ ለመረመረ ምስጋውን ለደህንነት ሃላፊው ለጌተቸው ረዳ ማድረሱን ግድ ይለዋል። ነገ ሌላ ያኮረፈ ሰው ተመሳሳይ መንገድ ቢከተል ይህ የኔ ሃሳብ የተበላበትና ባደባባይ የተገለጸ በመሆኑ እንደማይሰራ ካልነገርናቸው የህወሃት የደህንነት ሰዎች እንደገና ሞላ ላይ ሊሰሩበት እንደማይችሉ ማረጋገጫ የለም።

ሲጠቃለል የነጻነት ትግል ድርጅት መሪዎች ኩርፊያ በስልጣን ጥመኞች ልፊያ በጉርሻና በቁንጥጫ አይቆምም። የነጻነት ትግል የሚቆመው ነጻነት ሲመለስ ብቻ ነው።

ገብረጻዲቅ አበራ